# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ. ም
April 28, 2016

## ሜይ ዴይ - የሠራተኞች ቀን

በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር በየዓመቱ ሜይ ዴይ በመባል የሚታወቀው በሜይ ወር በመጀመሪያው ዕለት (ሚያዝያ 23) የሚከበረው የሠራተኞች ቀን ላብ-አደሮች ያለማሰለስ የሚያደርጉትን ትግል፣ እስካሁን ለኅብረተሰቡ ያበረከቱትን አስተዋጽዖና ወደፊትም የሚጠብቋቸውን ተግባራት ለመዘከር ነው። በዓሉ መከበር የጀመረው በ19ኛው ክፍለ-ዘመን በኢንዱስትሪ ባደጉት በምዕራብ አገሮች ላብ-አደሮች ግምባር ቀደምትነት ሲሆን፣ ዓላማውም ለመሠረታዊ የሠራተኛ መብቶች ተፈጻሚነት ነው። እነዚህም ዝቅተኛ የቤተሰብ ወጭን ሊሸፍን የሚችል ክፍያ ለማግኘትና ለሠራተኛ ጤንነት፣ አካልና ሕይወት ተስማሚ የሥራ ሁኔታ እንዲኖር፣ ትርፋቸውን ብቻ የሚያሳድዱት አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው አግባብ ያለው ክፍያ እንዲያደርጉ ለማስገደድ ነው። ይህ አመፃቸው በብዙ አገሮች የሚያረካ ባይሆንም ተፈጻሚነት ግን አግኝቷል።

ከ20ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በዓሉ ደምቆ ይከበር የነበረው ያኔ ኮሚኒስት በሚባለው ጎራ ተሰልፈው በሚገኙት አገሮች ላብ-አደሮች ነበር። ኢኮኖሚዋ በእርሻ ላይ በሚያተኩረው አገራችን የሠራተኛው መደብ አባላት ቁጥር ከሕዝቡ ቁጥር አንፃር ብዙ ነው ባይባልም፣ ከ20ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በጨርቃ ጨርቅ፣ በባቡር ሀዲድ፣ በአየር መንገድ፣ በሲሚንቶ ፋብሪካ፤ በቃጫ ፋብሪካ፣ በለስላሳ መጠጦችና በሆቴሎች፣ በትምባሆ ምርት፣ በዘመናዊ እርሻና በመሳሰሉት ዘርፎች የተሰማሩ ላብ-አደሮች ቁጥር በየዓመቱ እየጨመረ ሄዷል።

ሠራተኛው ከላይ ያነሳናቸውን መብቶቹን ለማስከበር በርካታ ማኅበራትን በማቋቋም ተጠናክሮ በንጉሡ ጊዜም ይሁን በደርግ ዘመን ለመብቶቹ ያልተቋረጠ ትግል አካሂዷል። በዚህ የትግል ጉዞውም በዋነኛ ድርጅቱ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌደሬሽን አማካይነት በርካታ የማይናቁ ድሎችን አስመዝግቧል። ትግሉ በሠራተኛው መብት ላይ

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009
Phone: 202- 241 2078
eprp_united@eprp-ihapa.com

ብቻ ሳይወሰን በአገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ባደረገው ተጋድሎም በርካታ ታሪካዊ አስተዋጽዖዎችን አስመዝግቧል። ለምሳሌ በንጉሡ ዘመን፣ በ1960 መግቢያ ላይ አገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በሶማሊያ ተስፋፊዎች በተወረረችበት ጊዜ የሠራተኛው ማኅበር ወረራውን ለመቋቋም የሚረዳ የገንዘብ መዋጮ ከማድረጉም በላይ ወደ ጦር ግምባር ለመዝመት ፈቃደኝነቱን ገልጿል። በደርግ ዘመንም የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች በማኅበራቸው አማካይነት የወታደሩ መንግሥት በሕዝባዊ መንግሥት እንዲተካ ያልተሳካ ቢሆንም እልህ አስጨራሽና ብዙ መስዋዕትነትን ያስከፈለ ትግል አድርገዋል።

በህወሓት/ኢህአዴግ ዘመን በዘር የተማከለ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚያንኳስስ፣ ጎሣንና ልዩነትን የሚያጎላ ፖሊሲ ተግባራዊ በሆነበት ጊዜም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ኢትዮጵያዊነትንና በላብ-አደርነታቸው ያሏቸውን የጋራ ጎሣ-ዘለል ችግሮች ማዕከል አድርገው የህወሓትን ዘረኝነት ታግለዋል፤ እየታገሉም ነው። ይህንን የተረዳው ህወሓት/ኢህአዴግ አሻጥር በተላበሰ መልኩ ተንኮሉን ማውጠንጠን ከጀመረ ዓመታት አስቆጥሯል። ለአንጋፋው የሠራተኞች ማኅበር ተለጣፊ የሠራተኞች ማኅበር ፈጠረለት። ይህ በአንድ ተቋም ላይ ሌላ ተለጣፊ አካል የመፍጠር ሽር በየፋብረካው የሠራተኞች ማኅበር ብቻ ሳይወሰን፣ በነፃ ሲቪክ ማኅበራትና የፖለቲካ ድርጅቶችም ተደጋግሞ የታየ የህወሓት መለያ ባህሪው ሆኗል።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሠራተኞች በብዙ ችግሮች ተጠምደው ይገኛሉ። ከደመወዛቸው አነስተኝነት የተነሳ ለቤተሰባቸው ምግብ ማቅረብ የሚችሉት በጣም ጥቂቶች ናቸው። በቂ የህክምና አገልግሎትና በሥራ ላይ ለሚደርስባቸው አደጋም በቂ የሕይወት ዋስትና የላቸውም። ለውጭ ኩባንያዎችና ለግል አሠሪዎች የሚሠሩ ሠራተኞችም መብታቸው የተሸራረፈ መሆኑን ማንም ይገነዘበዋል። የመንግሥት ሠራተኞች መብትም ለውጭ ኩባንያዎች ከሚሠሩት የተሻለ አይደለም። ህወሓት/ኢህአዴግ በልማት ስም የሚኩራራባቸውን መንገዶችና ህንፃዎች የሚሠሩ ላብ-አደሮች ሙሉ የሠራተኛ መብት እንደሌላቸው የሚታወቀው በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ አንድም የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ አለመቻላቸውን ስናይ ነው። ሠራተኛው ለመብቱ መታገሉ ዓለምአቀፋዊ ተቀባይነት ያገኘ መብቱ ሆኖ ሳለ፣ የሀገራችን ሠራተኞች የመብት

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**

ጥያቄ ሲያነሱ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የማፈኛ መሣሪያዎችን በመጠቀም መብታቸውን ረግጦና ድምፃቸውን አፍኖ እንደሚገዛ ይታወቃል። በመሆኑም በህወሓት/ኢህአዴግ ዘመን ሠራተኛው በንጉሡ ዘመን ከነበረው የድርጅት ጥንካሬ ጋር እንኳን ሲወዳደር በእጅጉ ወደኋላ ሂዶ፣ በተሰነጣጠቀና መብቱ በማይከበርበት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ግልጽ ነው።

ስለዚህም ሠራተኛው ኢትዮጵያዊ ክብሩንና የሠራተኛ መብቱን ለማስከበር በህቡዕና እንዳመቺነቱም በግልጽ በመደራጀት ከመታገል ሌላ ፍቱን መድኃኒት የለውም። በደርግ አፋኝ ሥርዓት ሕጋዊው የሠራተኛ ማኅበር ሲታገድ፣ ሠራተኛው እንደ ኢሕአፓ ካሉ ታጋይ ፓርቲዎች ጋር በመቀናጀት የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች አብዮታዊ ማኅበር (ኢላአማ)ን መፍጠሩን ያስታውሷል። አሁንም ወጣት ሠራተኞች ጊዜና ሁኔታ በፈቀደው መጠን እንደካሁን ቀደሙ ተደራጅተው መታገል ይገባቸዋል፣ እንደሚታገሉም እምነታችን ጽኑ ነው።

ኢሕአፓ (አንድነት) የዘንድሮን የ2008 የሠራተኛ ቀን ሲያስታውስ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሚደርስባቸውን የመብት ረገጣዎች ሁሉ ታሳቢ በማድረግ ነው። በዚህ አጋጣሚ በ1968 ዓ. ም የሠራተኞች ቀን ዋዜማና በዕለቱ በደርግ ነፍሰ-በላ አፋኞችና በሽረኮቻቸው የተጨፈጨፉትን አያሌ የኢሕአፓና የኢሕአወሊ (የወጣቱ ሊግ) አባላት ሰማዕትነታቸውን እንዘክራለን።

ሠራተኛው ይደራጃል! መብቱንና ኢትዮጵያዊነቱን ያስከብራል!

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009
Phone: 202- 241 2078
eprp_united@eprp-ihapa.com